# የሚሲዮናዊ የህይወት ታሪክ



**ጆርጅ ዊሻርት**
**የትውልድ ዘመን 1513 – 1546 ዓ.ም**
**የትውልድ ቦታ: ሞንትሮዝ፣ ስኮትላንድ**
**የሚሽን ቦታ: ስኮትላንድ**

ስለሰዎች ትምህርት ባስብ ኖሮ በሰዎች ታላቅ ምስጋና አግኝቻለሁ; ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለተሰጠኝ ስለ ቃልና ስለ እውነተኛው ወንጌል፥ ዛሬ በሰው እጅ መከራን የምቀበለው በሀዘን ሳይሆን በደስታ ልብና አእምሮ ነው። ጆርጅ ዊሻርት

ጆርጅ ዊሻርት በሞንትሮስ ውስጥ ከታወቀ ቤተሰብ የተወለደ እና በጥሩ ሁኔታ የተማረ ነበር። ከሉቨን ዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ሲሆን በሞንትሮዝ በሚገኝ ትምህርት ቤት ግሪክኛ አስተምሯል፤ በዚያም ተማሪዎቹን በግሪክኛ አዲስ ኪዳንን እንዲያነቡ በማድረጉ በሐሰት በመናፍቅነት ተከሰሰ። ስለዚህ፣ የፕሮቴስታንት ነገረ-መለኮትን የበለጠ ለመረዳት እየሞከረ አገሩን ጥሎ በመላ አውሮፓ ተዘዋወረ። በ 1542 በካምብሪጅ ኮርፐስ ክሪስቲ ኮሌጅን ተቀላቀለ ይህም በስዊስ እና በጀርመን የተሃድሶ አራማጆች ትምህርቶች ከፍተኛ ተጽዕኖ ስር እንዲሆን አድርጎታል።

እውነትን ለመስበክ አዲስ መነሳሳት በማግኘቱ በ1543 ወደ ስኮትላንድ ተመለሰ። ሕይወቱ አደጋ ላይ ወድቆ የነበረ ቢሆንም እና አንድ ጊዜ በሕይወቱ ላይ ከተደረገ ከባድ የግድያ ሙከራ ለጥቂት ቢያመልጥም በመላው ስኮትላንድ በመዞር የሊቀ ጳጳሱን ስህተተኛነትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድ አውግዟል። በአይርሻየር እያገለገለ ሳለ በዱንዲ ስለተከሰተ ወረርሽኝ ሰማ እና ወዲያውኑ ወደዚያ ቦታ ተመለሰ። ወረርሽኙ ሙሉ በሙሉ እስኪጠፋ ድረስ የተጠቂዎቹን መንፈሳዊ እና ጊዜያዊ ፍላጎቶችን እያገለገለ በዚያ ቆየ።ከወረርሽኝ ይልቅ ገዳይ ስለሆነው ኃጢአት እና ከኃጢአታቸውም እንዴት በእርሱ (በክርስቶስ) ግርፋት እንደሚፈወሱ ሰበከላቸው።

በዱንዲ በታማኝነት የሰራው ስራ ሊገድለው አሲሮ የነበረውን ካርዲናል ቢቶን እጅግ አስቆጣ። በዚህ ወቅት ነበር ጆን ኖክስ የተባለ ወጣት፣ በኋላ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መሪ የሆነው ዊሻርትን እንደ ግል ጠባቂው የተከተለው። በመጨረሻም ተይዞ ለፍርድ የቀረበው ዊሻርት ለቀረበበት ክስ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ በበቂ ሁኔታ መልስ ቢሰጥም ግን ሞት ተፈረደበት። ለከሳሾቹ በጸለየበት እና ይቅርታውን በተናገረበት የእንጨት መደገፊያ ላይ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ። ዊሻርት ረጅም የወንጌል አገልግሎት ባይኖረውም ትምህርቶቹ ግን በህዝቡ ላይ ዘላቂ የሆነ ተጽእኖ አድርገዋል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ለተቀጣጠለው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መሰረትን ጥሏል።

ወዳጅ ሆይ፣ የሐሰት ትምህርትን በመቃወም ሰዎችን ወደ እውነት እየመራህ ነው?
ጌታ ሆይ ፣ አስተዋይ አእምሮ እና ደፋር ልብ ስጠኝ። አሜን!
የሐሰት ትምህርቶችን ይቃወሙ።
እጣሪ:- ሚስተር ፔራ ስዋሚዳስ (የነፍስ አሸናፊዎች መጽሐፍ)